# የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 5/2012

ጥቅምት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## <u>መግቢያ</u>

ማናቸውም የሕዝብ አስተዳደር ስራ፤በሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲያዊ መርሆች ላይ ሊመሰረት እና በሕግመንግስቱ እውቅና ያገኙ መሰረታዊ መብቶችን ሊያከብር የሚገባው በመሆኑ፤

የፍትሕና የዴሞክራሲ ተቋማትን የማሻሻል ሂደት ህዝብንና ባለሙያዎችን ባሳተፈ መልኩ ተግበራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የፍትህና ዴሞክራሲ ተቋማት አገልግሎት ውጤታማነትና የሕዝብ ፍላጎትን በማርካት ረገድ ያሉትን ችግሮች በየወቅቱ በመለየት፤ ተቋማዊ የለውጥ ፕሮግራሞችን መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የለውጥ ፕሮግራሞችን ለመንደፍና አፈጻጸማቸውን ለመገምገም፤ መረጃንና፤ ልምድን፤ አሳታፊና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መሰብሰብና መተንተን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 8/2/ሰ/ መሰረት ይህንን መመሪያ አዉጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "**በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር** 5/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

1. "**የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ**" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 መሰረት የተቋቋመው ጉባኤ ነው።

2. "**ፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ**" ማለት በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 3 መሰረት የተቋቋመው ተቋም ነው።

3. "**ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ**" ማለት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃ ህግ ሀላፊ ነው።

4. ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

### 3. መቋቋም

1. የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባኤ" እየተባለ የሚጠራ) በፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ስር በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

2. የጉባኤው ተጠሪነት ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ነው፡፡

### 4. ዓላማዎች

ጉባኤው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ዙሪያ መረጃና ጥናትን መሰረት በማድረግ ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሙያዊ ምክር መስጠት፤

2. በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሚረቀቁ ህጎች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢውን እገዛ ማድረግ፤

3. የህግና የፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወን አቅጣጫዎችን እና የመፍትሄ ሀሳቦችን ማመንጨት፤

### 5. <u>ሥልጣንና ተግባራት</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በህግና ፍትህ ጉዳዮች ላይ መሻሻል ያለባቸውን ተቋማት፣ አሰራሮችና ህጎች በማመላከት ፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ያማክራል፣

2. የፍትሕና ዴሞክራሲ ተቋማት ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ህዝብን የሚያረካ አገልግሎትን እየሰጡ መሆኑን ለመከታተልና ለመገምገም፤ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

3. የክትትልና የግምገማ ማዕቀፉን፣ መረጃና ጥናትን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የፍትህና ዴሞክራሲ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታና ችግሮችን ይለያል፣ የመፍትሔ ሃሳቦችን እና ረቂቅ ህጎችን ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ያቀርባል፤

4. የምክክርና ዉይይት መድረኮች ያዘጋጃል፣ ይመራል፡፡

5. ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበውን የምክር ቤቱን የስራ ፕሮግራም ያከናውናል፤እንደአስፈላጊነቱም ያሻሽላል፡፡

## 6. <u>የጉባኤው አባላት</u>

1. ጉባኤው አስራ ሶስት አባላት ይኖሩታል፤

2. የጉባኤው አባላት በዚህ መመሪያ የተሰጣቸውን ሃላፊነቶች ሲያከናዉኑ፤ ተገዢነታቸው ለሕሊናቸውና ለሙያቸው ስነ-ምግባራቸው ብቻ ነው፤

3. ማናቸውም የጉባኤው አባል ከተሰጠው ሃላፊነት ጋር የሚጋጭ የግል ጥቅምና ግንኙነቶች ካጋጠመው ራሱን ከጉዳዩ እንዲያገል በምክር ቤቱ ሊወሰን ይችላል፤

4. የጉባኤው አባላት በፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ይመረጣሉ፤

## 7. <u>የስራ ዘመን</u>

የምክር ቤቱ አባላት የስራ ዘመን ለሶስት አመት ይሆናል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የስራ ዘመናቸውን ሊያራዝም ይችላል፡፡

## 8. <u>የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

1/ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

2/ የምክር ቤቱ ውሳኔ በተቻለ መጠን በጋራ ወይም በተባበረ ድምፅ ይህም ሳይቻል ሲቀር በአብላጭ ድምጽ ይተላለፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰባሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 9. የምክር ቤቱ አሰራር

1. ጉባኤው በጽህፈት ቤቱ የሙሉ ጊዜ ሰራተኞች ይታገዛል፡፡

2. ጉባኤው የተለያዩ የስራ ቡድኖችን በማቋቋም መረጃ የመሰብሰብና ጥናት የማካሄድ፣ ረቂቅ ሕጎች የማዘጋጀት የምክክር መድረኮችን የማዘጋጀት አስተያየት የመቀበልና የማደራጀት ስራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል፡፡

2. ጉባኤው በስራ ቡድኖቹ የሚከናወኑ ጥናቶችና የሚዘጋጁ ረቂቅ ሕጎች ላይ በመወያየት ተጨማሪ መረጃና ጥናት ሲያስፈልግ የስራ ቡድኖቹ እነዚህን እንዲያቀርቡለት ማድረግና ሌላም አስፈላጊውን የስራ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 10.የጉኤው ጽህፈት ቤት

1. ጉባኤውንና የስራ ቡድኖችን የሚያስተባብርና የሚያግዝ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ጉባኤ ፅህፈት ቤት (ከዚህ በኂላ "**ፅህፈት ቤት**" እየተባለ የሚጠራ) በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ውስጥ ይደራጃል፡፡

2. ፅህፈት ቤቱ ቋሚ ሰራተኞች የሚኖሩት ሲሆን አስፈላጊው ግብአትም በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይሟላለታል፣

3. የጽህፈት ቤቱ ሃላፊና ምክትል ሃላፊ በጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ይመደባል፤3. የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኖ በቀረበው መሰረት ይሆናል፡፡ ሆኖም የጽህፈት ቤቱ ሃላፊ ከምክር ቤቱ ሰብሳቢ ጋር በመነጋገር ጽህፈት ቤቱን በተለየ መልኩ ሊያደራጀው ይችላል፡፡

## 11.የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሀላፊነት

የፌዴራል ጠቅላይ አቃቢ ሕግ፤

1. ለጉባኤው፣ ለስራ ቡድኖቹ እና ለፅህፈት ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2. የጉባኤውና የስራ ቡድኖች አባላት ለሚያቀርቡት ነጻ ሙያዊ አገልግሎት እውቅና ይሰጣል፡፡
3. በጉባኤው የሚቀርቡ ረቂቆችንና ምክረ ሃሳቦችን በመንግስት መደበኛ አሰራር መስረት በተቻለ ፍጥነት ውሳኔ ይሰጣል፥ ወይም ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አስቀርቦ ያስወስናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዮ ልዩ ድንጋጌዎች

**12. <u>የተሻሩ ህጎች</u>**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ፣ ማንዋል እና የአሰራር ልምድ ይህ መመሪያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

**13. <u>መመሪያዉ የሚፀናበት ግዜ</u>**

ይህ መመሪያ በስራ ሂደቶች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ...ቀን 2011ዓ/ም

ብርሀኑ ፀጋዬ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ